# ኦሮሞን እንደ እንስሳ በበረት ማኖር አይቻልም

ስፈልግሽ ኩምሳ

ሰሞኑን በጄ/ል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ ያስተላለፈው ውሳኔ አቧራ ከማስነሳት አልፎ ሱናሚ እየቀሰቀሰ ነው። በድረገጾች የሚወጡት ጽሁፎች፣ በፓልቶኮች የሚወረወሩት አስተያየቶች በአብዛኛው ያስደነግጣሉ፤ ያስፈራሉ፤ የሚያስደስቱ ባይጠፉም። የማይምን መጋረጃ የቦጫጨቀውም ሆነ የማይምን መጋረጃ በደንብ ያልቀደደው፣ በስሜት ሰክሮ ፣ የአሁኑን ትውልድ ብቻ ሳይሆን የሚቀጥለውንም ትውልድ የሚያቃጥል፣ የመርዝ ጋዝ ጭስ ይረጫል። ይህ ጭስ ተስፋፍቶ ተስፋፍቶ እንደ ሩዋንዳ እንደሚያፋጅን ለመረዳት የቻለው ሰው ጥቂት ነው። አብዛኛው ሰው ከአፉ መርዝ መትፋቱን እንጅ መርዙ የት ይደርሳል፣ ምን ጉዳት አለው የሚለውን አያስተውልም። እናም ፓልቶኮቻችን፣ ጸረ አረም መሆን ሲገባቸው ጸረ ሰው ሆኑ። አብዛኞቹ።

እነ ጄ/ል ከማል ገልቹ በኢትዮጵያ ስር ሆነን ነጻነታችንን እናውጃለን አሉ። ተቀራኒዎቻቸው እነዳውድ ኢብሳ ደግሞ እነ ጄ/ል ከማልን "የቅኝ ገዢዎች የአቢሲኒያውያን ተላላኪዎችና ጉዳይ ፈጻሚዎች" ናቸው ሲሉ አወገዙዋቸው። የኦሮሞ ምሁራን የተባሉትም፣ ነገሮችን በሰከነ መንገድ ከማየት ይልቅ አሁንም ለትውልድ የሚሸጋገር መርዝ እየተፉ ነው። የኦሮሞ ምሁራን የተባሉት ሁሉ አንድ ትንሽ ነገር መገንዘብ አቅቶአቸዋል። ኤርትራ ለምን ተገነጠለች? ከኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት የተሻለ ሀይል ስለነበራት ነው። ከዚያ ያነሰ ሀይል ቢኖራት ኖሮ አትገነጠልም ነበር። ኦነግ ተዋግቶ ኦሮሚያን የማይገነጥለው ቅዱስ ስለሆነ አይደለም፤ ስላልቻለ ብቻ ነው። በቃ የተዋጋ እየመሰለው እየተወጋ ነው የተዳከመው።

ኦነግ ኦሮሚያን ልገንጥል ብሎ ከተነሳ የማንንም ፈቃድ መጠየቅ አያሻውም። ሀሳቡን በዛ ያለው ህዝብ ሲቀበልለት ጉልበት ያገኛል። ጉልበት ሲያገኝ ጥሩ ተዋጊ ያገኛል፤ ያሸንፋል። የተሸነፈ ህዝብ በአሸናፊው ፍላጎት ላይ ሊወስን አይችልም። የኢትዮጵያ ህዝብ ኤርትራ እንድትገነጠል ፍላጎት አልነበረውም፣ ነገር ግን የኤርትራን እና የኢትዮጵያን መንግስታት የሚያሸንፍበት ሀይል አልነበረውም። ሳይወድ በግድ ተቀበለ።

እነ አሰፋ ጃለታ፣ ዳውድ ኢብሳም ሆኑ ጃዋር ሙሀመድ ማወቅ ያለባቸው ሀቅ ይህ ነው። በወረቀት ላይ ከመንጫጫት እና በባዶ ሜዳ ቡራ ከረዩ ከማለት ጉልበታቸውን አሳይተው ኦሮሚያን ይገንጥሉ። አንድ በእርግጠኝነት መናገር የምችለው በእነ ዳውድም ሆነ በእነ ጃዋር እድሜ ይህ የሚሆን አይደለም። ብዙ ምክንያቶችን ላቀርብ እችላለሁ። ኦሮሞ በታሪኩ ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የተሳሰረ ነው። ኦሮሞ ደሙ ጎንደር፣ ጎጃም ወሎ፣ ሸዋ ውስጥ አለ። የኦሮሞ ደም ደቡብ ፣ ሶማሊ ፣ አፋር ውስጥ አለ። ኦሮሞ በተስፋፋባቸው አካባቢዎች ከሌላው ህዝብ ጋር እየተዋለደ እንጅ የእኔ ደም የአይሁድ ነው ብሎ፣ ግልገል ሱሪውን ቆልፎ፣ አልተቀመጠም። ንጹህ አማራ የሚባል እንደሌለ ሁሉ ንጹህ ኦሮሞ የሚባልም የለም። ኦሮሞ በተስፋፊነቱ ምክንያት አንድ የመሆን ጉልበቱን አዳክሞአል። የሸዋ ኦሮሞ ከወለጋው፣ ከጅማው ፣ ከአምቦው ወዘተ ይለያል። ኦሮሞ እርስ በርሱ ካለው

ትስስር ይልቅ ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለው ትስስር ይጠነክራል። ይህ ደግሞ የኦሮሞን ሰፊ አስተሳሰብ ያመለክታል።

እነዳውድ ኢብሳ ጠባብ ቢሆኑም ኦሮሞ ግን ጠባብ አይደለም። ግሎባላይዜሽንን ገና ጥንት ያስፋፋው ኦሮሞ ነው። በሄደበት ይወልዳል፣ የደረሰበትን አካባቢ ባህል ይወርሳል፣ የራሱንም ያወርሳል። ኦሮሞን በኦሮሚያ ወይም በኦሮማማ ታጥረህ ተቀመጥ ብትሉት አይሆንለትም። ተዋህጅ ነው። ሰውን በሰውነቱ እንጅ በዘሩ የሚቆጥር ህዝብ አይደለም። አጼ ሱስንዮስን አሳድጎ ሚስት አጋብቶ ለስልጣን ያበቃ ነው። ከጎንደር ወይዛዝርት ጋር እየተጋባ ዘሩን የተከለ ነው። በአማራ ግዛት የኦሮሞ ደም አለኝ ማለት ያኮራል እንጅ አያሳፍርም። የኦሮሞ ደም ያለባቸው ሰዎች ናቸው፣ የባላባት ዘር እየተባሉ የሚጠሩት።

እነዳውድ ኢብሳ አርባ አመት ሙሉ ቢታገሉ ቢታገሉ እድሜያቸውን ከመጨረስ ውጭ ምንም መፈየድ ያልቻሉት የኦሮሞን ህዝብ ባህሪ ስላልተረዱ ነው። ኦሮሞን እንደ ስድስት ኪሎ አንበሶች አጥሮ ማስቀመጥ ወይም እንደ ከብቶች በበረት ማኖር አይቻልም። ኦሮሞ ዛሬ ቢገነጠል፣ ነገ ቀድሞ የሚያፈርሰው እርሱ ራሱ ነው። ኦሮሞ የአማራን ሴት አይቶ ልቡ አይጨክንም። የአማራ ሴት የኦሮሞን ወንድ አይታ አታልፈውም። አማራ ክልል ውስጥ የኦሮሞ ባል ለማግባት የማትፈልግ ሴት የለችም። ኦሮሞ ደግ ነው፤ ሚስቱን የሚንከባከብ ዲሞክራት ነው ይባላል። በደርግ ፍጻሜ ጊዜ ብዙ ኦሮሞዎች በአማራ ክልል ሴቶችን እያገቡ ተቀምጠዋል። ሴቶቹም በኦሮሞ ባሎቻቸው ይኮራሉ። እስኪ ለመሆኑ ከሌላ ዘር ያልተጋባው ኦሮሞ እጁን ያውጣ?

አሁን በፓልቶኮች የሚረጩት የመርዝ ጋዞች ይህን ሀቅ ለመሸፈን ከቶ አይቻላቸውም። ምንም ይሁን ምን ይህን እውነታ ተረድቶ በዚህ እውነታ ስር አላማን ማራመድ ካልተቻለ ፣ እነዳውድ ኢብሳ ፣ በህይወት ካሉ፣  ከአርባ አመት በሁዋላም ራሳቸውን በቆሙበት ያገኙታል። ጀ/ል ከማል ገልቹ ቅዱስ ስለሆነ አይደለም የመገንጠል ጥያቄውን ያነሳው። ይህን እውነታ ተደርቶ ነው። ሌሎችም ምሁራን ሰዎችን ከመዝለፍ፣ መርዝ ከመርጨት ተቆጥበው ይህን እውነታ ቢረዱና በሰከነ ሁኔታ ፖለቲካቸውን ቢያራምዱ፣ ለኦሮሞ ህዝብ ፍላጎት ተገዙ ማለት ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን በቅድሚያ የሚተፉትን መርዝ ማቆም ሲችሉ ነው።